የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግሥት

ልሣነ- ሕግ ጋዜጣ

LISANE HIG GAZETA

OF THE BENISISHANGUL GUMUZ REGIONAL STATE

| ፲፭ኛ ዓመት ቁ ጥር 84<br>ሐምሌ 2001<br>አሶሳ | በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ<br>መንግሥት ምክር ቤት ጠባቂነት<br>የወጣ | 15th year No.84<br>July, 2009<br>Assosa |
|---|---|---|

**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር 84/ 2001 ዓ/ም
መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥን ለመተግበር
የወጣ አዋጅ

**Contents**

**Proc. No 84/2009**
**Benshangul /Gumuz Regional state's Business process Reengineering proclamation**

## አዋጅ ቁጥር 84/2001ዓ/ም መሠረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናትን ለመተግበር የወጣ አዋጅ

በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል የመንግሥት መ/ቤቶች ውስጥ እየተሠራባቸው ያሉ ህጐችና የአሠራር ልምዶች በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት የተገኙ አዳዲስ አሠራሮችንና አደረጃጀቶችን ለመተግበር የማያስችሉት ሆነው በመገኘታቸው፣

በክልሉ ውስጥ ተጠያቂነት የሚያስከትል፣ ግልጽነትን የተላበሰ፣ አሳታፊ ፈጣንና ቀልጣፋ አገልግሎት ለኀብተሰቡ በብቃት በመስጠት ከድህነት ለመውጣትና መልካም አስተዳደርን ለማስፈን የሚደረገው ጥረት ለማሳካት መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናትን ውጤታማ በሆነ መልክ ተግባራዊ ለማድረግ ምቹ ሁኔታ መፍጠር በማስፈለጉ፣

መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት ተግባራዊ ሲሆን የመልካም አስተዳደር መርሆዎችንና የሕግ የበላይነትን መሠረት ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፣

በጥናቱ የተደረሰባቸውን የአሠራርና የአደረጃጀት ማሻሻያዎች በቋሚነት ተግባራዊ ለማድረግ በሥራ ላይ ያሉትን ሕጐች ከሙከራ ትግበራ በኀላ ማሻሻል በማስፈለጉ፣

## Proclamation No.84/2009 A proclamation to Implement the Business process Reengineering

Whereas, it is believed that the existing laws and practices hinder effective and efficient implementation of outcomes of the business process reengineering study in the governmental institution of the Regional state;

Whereas, the regional state desired to create fertile ground for effective implementation of the outcomes of the business process reengineering study and thereby to be successful in getting-rid of poverty by rendering accountable, transparent, fast and effective service to the public;

Whereas, it has become necessary to rely on the fundamental principles of good governance and rule of law in the course of implementing the business process reengineering;

Whereas, it is believed that permanent implementation of outcomes of the business process reengineering study demands amendment of the existing laws after pilot testing the process and structure.

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ምክር ቤት በተሻሻለው የክልሉ ህገ መንግሥት አንቀጽ ፵፱ (፫) (፩) መሠረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል፡፡

Now, therefore, in accordance with article 49(3)(1)of the revised constitution proclamation, it is her by proclaimed as follows:

## ፩.አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግሥት መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት መተግበሪያ አዋጅ ቁጥር 84/2001ዓ/ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 1.Short Title

This proclamation may be cited as the Benishangul/Gumuz regional State's "BUSINESS process Reengineering Implementation" proclamation No 84/2009

## ፪.ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ፣

፩. "ምክር ቤት" ማለት የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ም/ቤት ነው፡፡

፪. "መሠረታዋ የሥራ ሂደት ለውጥ" ማለት በክልሉ የመ/ቤቶችን የሥራ ሂደት በማደራጀት ፈጣንና ቀልጣፋ አገልግሎት ለመስጠት እንዲቻል ከተለያዩ የሥራ ሂደቶች ያካሄደውን ጥናት ውጠት የሚያመላክት ሰነድ ነው፡፡

፫. "ካቢኔ" ማለት የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል መንግሥት ካቢኔ ማለት ነው፡፡

፬. "መሥሪያ ቤት" ማለት ቢሮ፣ ፍ/ቤት፣ ኮሚሽን፣ጽ/ቤት፣ ባለሥልጣን፣ ተቋም፣ኤጀንሲ ወይም ማንኛውም ሌላ የክልሉ መንግሥት በአዋጅ ወይም በደንብ ያቋቋመው የሕዝብ አገልግሎት መስጫ ተቋም ነው፡፡

## 2. Definition

Unless expressed otherwise, in this proclamation:

1. "Council" shall mean the council of the Benshangul /Gumuz Region.
2. "Business process Reengineering" shall mean the outcomes of the study to organize the tasks of governmental institutions of the regional state in different job processes so that to enable them render effective and efficient public service.
3. "Cabinet" shall mean the executive council of the Benshangul /Gumuz Regional state.
4. "Office" shall include Bureau, Court, commission, office, Authority, Institution, Agency or any other institution of the Regional state established by proclamation or Regulations that renders service to the public.

## ፫.የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ አዋጅ ተፈጻሚ የሚሆነው መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናትን በማጠናቀቅ ተግባራዊ በሚያደርጉና በመሙሉም ሆነ በከፊል በክልሉ መንግስት በጀት በሚተዳደሩ መ/ቤቶች ላይ ብቻ ይሆናል፡፡

## 3. Scope

This proclamation shall be applicable only to the government office that fully or partially run bu the Regional State budget and those which implement the business process reengineering after accomplishing the phase of study.

፬ የመሰረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥን ስለመተግበር

የመንግሥት መ/ቤቶች አገልግሎት አሰጣጥ መሠረታዊ መሻሻል የሚጠይቅ በመሆኑ የክልሉ መንግሥት በዚህ አቅጣጫ የሚፈለገውን ለውጥ ለማምጣት ወስኗል። ይህም የሥራ ቅልጥፍናና ውጤታማነት በማረጋገጥ፣ አገልግሎት በመስጠትና በመቀበል ሂደት ላይ የሚያጋጥሙ ችግሮችን ማቃለልና መልካም አስተዳደርን፣ ኢኮኖሚያዊና ማኀበራዊ ዕድገትን በክልሉ ለማፋጠን የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ በዚህ አዋጅ እውቅና አግኝቶ ተግባራዊ ይሆናል።

፭. **ደንብ የማውጣት ሥልጣን**

፩. የመስተዳድሩ ካቢኔ ለዚህ አዋጅ ሙሉ ተፈጻሚነት የሚያስፈልግ ዝርዝር ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

፪. የክልሉ አቅም ግንባታ ማስተባበሪየ ቢሮ ዝርዝር የአፈጻጸም መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።

፮. **የመሸጋገሪያ ድንጋጌ**

፩. በክልሉ መንግሥት ሥር የሚኙ የመንግሥት መ/ቤቶች መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት አጠናቀው ጥናቱ በክልሎ ምክር ቤት ወይም አግባብ ባለው አካል ጸድቆ ለውጡን ሲተገብሩ መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ በተመለከቱ ጉዳዮች በሥራ ላይ ካሉ ማናቸውም አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሠራር ጋር ግጭት ቢፈጠር መሠረታዊ ሥራ ሂደት ለውጥን ለመተግበር የወጡ ሕጐች እና በጥናት የተገኘው አዲስ አሠራርና አደረጃጀት ተፈጻሚነት ይኖረዋል።

፪. በዚህ አዋጅ ትግበራ ሂደት የሚፈጸሙ ማናቸውም የሕግ ድንጋጌ መተላለፍ አግባብነት ባለው ህግ መሠረት ታይቶ ውሣኔ የሚሰጣቸው ይሆናል።

፯. **አዋጁ በሥራ ላይ የሚቆይበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በሥራ ላይ የሚቆየው በክልሉ ም/ቤት ከጸደቀበት ከ ፲፩/፲፪/2ሺ1 ዓ/ም ጀምሮ ለሁለት ዓመት ብቻ ነው።

፰. **አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ ከ ፲፩/፲፪/2ሺ1ዓ/ም ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አሶሳ

ሐምሌ 2001ዓ/ም

አህመድ ናስር

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግሥት

ኘሬዝዳንት

**4.** Implementation of Business process Reengineering

The state of service delivery in government offices Calls for fundamental improvement.

The Regional Government is committed to bring about such an improvement by ensuring efficiency and effectiveness of service delivery in the region thus reducing the problem of providing and receiving services and there by facilitating good governance, economic and social development of the region. And therefore, it is imperative to implement business process reengineering (BPR) by acknowledging this proclamation.

**5. Issuance of Regulation**

1. The cabinet of the Regional State may issue detail regulation for the proper implementation of this proclamation.
2. The Regional capacity Building coordination Office may issue detail directive.

**6. Transitory provision**

1. Any proclamation, regulation, directive or customary practice that does not go in conformity with laws and results of study of the Business process Reengineering shall not be applicable as regards matters covered there in.
2. Any violation of laws during implementing this proclamation shall be adjudicated according to the existing laws.

**7. Duration**

This proclamation shall remain force only for two years as of its promulgation by the Regional State.

**8. Effective Date**

This proclamation shall come into force as of the 17th day of August 2009

Assosa

August, 17, 2009

Ahmed Nasir

Benishangul/Gumuz Regional State' President